ህዳር 7 ቀን 1998

መ/ቁ.14699

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሀይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ተገኔ ጌታነህ

4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢንጂነር ወርቁ መኮንን የአመልካች ወራሾች ሞግዚት ወ/ሮ ገነት ኤርሲዶ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የቦሌ ክ/ከተማ ገቢዎች መምሪያ - ነ/ፌጅ ገዛኸኝ ኢርኮ ቀረበ

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሲሆን አመልካች በይግባኝ አቤቱታቸው ገቢ ለመፍጠር ወጪ ያደረጉት ገንዘብ በወጪነት ሳይያዝ ግብር እንዲከፍሉበት የተወሰነ በመሆኑ ይኸው ገንዘብ በወጪነት እንዲያዝላቸው የጠየቁ ሲሆን ጉባኤውም ወጪ ለመውጣቱ ማስረጃ የቀረበ በመሆኑ በወጪነት ሊያዝላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሣኔ ያፀናው ቢሆንም የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ግን ለድርጅቱ ወጥተዋል የተባሉት ወጪዎችን ለማረጋገጥ የቀረቡት ማስረጃዎች በግብር ሕጉ በተደነገገው መሠረት ትክክለኛ የሆኑ ሰነዶች ስላልሆኑ በወጪነት ሊያዙ ስለማይገባ ግብር ይከፈልባቸው በማለት ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም የቀረቡት ሰነዶች ወጪዎቹ ገቢን ለመፍጠር የወጡ ወጪዎች ለመሆናቸው ለማረጋገጥ ብቃት ያላቸው ሰነዶች በመሆናቸው በወጪዎቹ ላይ ግብር እንዲከፈል መደረጉ የህግ ስህተት ነው የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ደረሰኞቹ በግብር ሕጉ መሠረት የተሰሩ ትክክለኛ ሰነዶች ስላልሆኑ ተቀባይነት ሊያገኙ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከላይ ከተመለከተው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን ይህ ችሎት አመልካች ግብር እንዲከፈሉ የተሰጠው ውሣኔ የገቢ ግብርን ለማስከፈል የወጣውን አዋጅ መሠረት ያደረገ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በገቢ ግብር አዋጁ መሠረት ግብር የተጣለበትን ገቢ የሚሰበስብ ማንኛውም ሰው በአዋጁ በተመለከተው መሠረት ከጠቅላላው ገቢ ላይ ገቢውን ለመፍጠር የወጡ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ በሚገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ ግብር የመክፈል ሃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም ግብር ከፋይ ገቢን ለመፍጠር ያወጣውን ወጪ ትክክለኛነት ተቀባይነት ሊያገኙ የሚገባቸው ሰነዶች በማቅረብ ወጪዎቹን የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ የግብር ሰብሳቢው ባለስልጣንም የሚቀርቡለትን ሰነዶች ወጪዎች በትክክል ገቢን ለመፍጠር የወጡ ለመሆናቸው የሚያስረዱ ትክክለኛ ሰነዶች ስለመሆናቸው የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፡፡ የቀረቡለት ሰነዶች ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሃላፊነት የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት እንደመሆኑ መጠን መ/ቤቱ የሰነዶቹን ትክክለኛነት ሊያረጋግጥ የሚገባው እንዴት ነው የሚለው በቀጣይነት መታየት ይኖርበታል፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ የወጣው ግብር ከፋዩ ግብር በተጣለበት ገቢ ላይ የሚፈለገውን ትክክለኛ ግብር እንዲከፍል ለማድረግ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀውም ግብር የሚከፈልበት ገቢ ገቢውን ለመፍጠር የወጣው ወጪ ከጠቅላላ ገቢው ላይ ከተቀነሰ በኋላ በሚገኘው ትርፍ ላይ ብቻ በመሆኑ ገቢን ለመፍጠር የወጡ ወጪዎች ሳይቀነሱ በጠቅላላው ገቢ ላይ ግብር እንዲከፈል ማድረጉ የአዋጁን አላማ የሚጻረር ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የቀረቡትን ሰነዶች በሙሉ መቀበሉም ግብር ሊከፈልበት የሚገባው ገቢ እንዲቀንስ የሚረዳ ስለሚሆን የሚቀርቡ ሰነዶች ትክክለኛነት በጥንቃቄ መረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀጽ 29 ለባለስልጣኑ የሚቀርቡ የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች ውስጥ የሚሰፍሩ ሂሳቦች ትክክለኛ በሆኑ ሰነዶች /ቫውቸሮች/ መደገፍ እንዳለባቸው ያዛል፡፡ ይህ የአዋጁ ድንጋጌ ትክክለኛ ሰነዶች እንዲቀርቡ የፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ወጪዎቹ በቀጥታ ገቢን ለመፍጠር ስለመውጣታቸው በበቂ ሁናቴ ለማረጋገጥ እና ግብር ከፋዩ ሃሰተኛ ሰነድ በማቅረብ የግብር ግዴታውን እንዳይሸሽ ለመቆጣጠር እንጂ የሰነዶቹን አዘገጃጀት ሥነ - ሥርዓት መሟላት አለመሟላቱን ለመቆጣጠር ባለመሆኑ የሰነዶቹ ይዘት ሊታይ የሚገባው ከዚሁ የአዋጁ አላማ አንፃር ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም ለመ/ቤቱ የቀረቡት ሰነዶች ወጪ ለመውጣቱ የሚያሳዩ በቂ ሁኔታዎችን እስከያዙ ድረስ መ/ቤቱ ሰነዶቹ ሲዘጋጁ ሊሟሉ ያስፈልጋል የሚላቸው ስርዓቶች /ፎርማሊቲዎች/ በሙሉ ባለመሟላታቸው ብቻ ሰነዶቹን ውድቅ ማድረግ ተገቢ አይሆንም፡፡ በእርግጥ የሥርዓቶቹ መሟላት ወጪው መውጣቱን ለማረጋገጥ የተሻሉ ማስረጃዎች ሊያደርጋቸው ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም ሰነዶቹ መ/ቤቱ እንዲሟሉ የሚፈልጋቸው ሥርዓቶች ባያሟሉ እንኳን ወጪ ለመውጣቱ ሊያረጋግጡ የሚችሉ በቂ ሁኔታዎችን እስካሳዩ ድረስ ተቀባይነት ሊያገኙ የማይችሉበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

ወደ ተያዘውም ጉዳይ ስንመለስ አመልካቹ የህንፃ ተቋራጭ ሲሆኑ ግብር የተጠየቁትም ለሚሰሩት የግንባታ ሥራ እንደሆነ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ግብር

የተጣለባቸው ይህንኑ ሥራ አከናውነው ገቢ አግኝተዋል በማለት ከሆነ አመልካች ግንባታውን ማከናወናቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህን የሥራ ዘርፍ ለማከናወን ደግሞ አሸዋ፣ ድንጋይ የመሳሰሉት ጥሬ እቃዎች መጠቀማቸው እንደማይቀር አከራካሪ አይሆንም፡፡ አከራካሪ ሊሆን የሚችለው ግብር የተጣለበትን የግንባታ ሥራ ለመስራት እነዚህ ጥሬ እቃዎች መግዛት አለመግዛታቸው ሳይሆን ግንባታውን ለመስራት ጥቅም ላይ የዋሉት ጥሬ እቃዎች መጠን እና ዋጋቸው ነው፡፡ አመልካች ሥራቸውን ለማከናወን ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ጥሬ እቃዎች የገዙት ከገጠር የአገሪቱ ክፍል ለመሆኑ የገለፁትን እውነታ ተጠሪ ክርክር እንዳላቀረበበት ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በገጠር የሃገሪቱ ክፍል ለሚደረግ ሽያጭ ደግሞ ማህተም ያለው ደረሰኝ ማግኘት ከባድ በመሆኑ የወጣውን ወጪ ለማረጋገጥ የቀረበው ሰነድ ነጭ ወረቀት መሆኑን አመልካቹ ገልፀዋል፡፡ ግብር ሰብሳቢው መ/ቤትም የቀረበለትን ሰነድ ውድቅ ያደረገውም ሰነዱ ማህተም ያልተደረገበት ነው በሚል ብቻ እንጂ ግብር የተጣለበትን ገቢ ለመፍጠር እነዚህ ጥሬ እቃዎች አልተገዙም ወይም ወጪው የተጋነነ ነው በማለት አለመሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ በዚህ በኩል ያቀረበው ክርክር ቢኖር ኖሮ ከፍ ሲል እንደተባለው ጉዳዩ አከራካሪ ሊሆን ይችል ነበር፡፡ በተጠሪ በኩል ግን እንደዚህ አይነት ክርክር አልቀረበም፡፡ በእቃዎቹ ዋጋና መጠን ላይ ክርክር ሳይቀርብ ወጪ መውጣቱ በተረጋገጠ ጉዳይ ላይ ሰነዱ ማህተም የለውም በሚል ብቻ ሰነዱን ውድቅ ማድረጉ ደግሞ በወጣ ወጪ ላይ ግብር እንዲከፈል የማድረግ ውጤት ስለሚኖረው አዋጁን የሚቃረን አፈፃፀም ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ ለመኪና የሰሌዳ ቁጥር ከመስጠቱ በፊት የሻንሲ ቁጥር እየተመዘገበ ጥገና ሲደረግ የነበረ በመሆኑ የቀረበው የታርጋ ቁጥሩ ያልተመዘገበበት ደረሰኝ መሆኑን መዝገብ ያመለክታል፡፡ በዚህ ደረሰኝ ላይ የሰፈረው የሻንሲ ቁጥር የአመልካች መኪና ለመሆኑ ማረጋገጡን ግብር ሰብሳቢው መ/ቤትም አይከራከርም፡፡ መታየት ያለበት ደግሞ የቀረበው ሰነድ ለአመልካች መኪና ጥገና የተደረገ መሆኑን ማረጋገጡ እንጂ የግድ የመኪናው ሰሌዳ ቁጥር መፃፉ ሊሆን አይገባም፡፡ የሻንሲ ቁጥሩም ቢሆን ከታርጋ ቁጥሩ የበለጠ መኪናው የአመልካች መኪና ለመሆኑ የማረጋገጥ ብቃት አለው፡፡ በመሆኑም ደረሰኙ ጥገና የተደረገለት መኪና የትኛው መኪና ለመሆኑ ማረጋገጥ እየቻለ የታርጋ ቁጥሩ ባለመግለጹ ብቻ ገቢን ለመፍጠር የወጣው ወጪ ላይ ግብር እንዲከፈል ማድረጉ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ለነዳጅ



የወጣውን ወጪ በተመለከተም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ነዳጅ ለመቀዳቱ በተሰጠው ደረሰኝ ላይ የተመዘገበው የመኪናው ታርጋ ቁጥር የአመልካች መኪና ታርጋ ቁጥር ላለመሆኑ የቀረበ ክርክር ሳይኖር የባለቤቱ ስም ባለመፃፉ ብቻ ሰነዱ ውድቅ ሊደረግ የሚገባባት ምክንያት የለም፡፡

በአጠቃላይ ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ሕጉ የሚያዘው ግብር ከፋዩ የተጣለበትን ግብር የመክፈል ግዴታውን ሳይወጣ እንዳይቀር ለመቆጣጠር በመሆኑ ሰነዶቹ በበቂ ሁኔታ ወጪ መውጣቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ነገሮች ከያዙ በሰነድ አዘጋጃጀት ላይ የተለያዩ ፎርማሊቲዎች ባለመሟላታቸው ብቻ ሰነዱን ውድቅ ማድረጉ፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ውጤቱ ከግብር ሕጉ በመውጣት ግብር እንዲከፈልበት ባልተጠየቀ ገንዘብ ላይ ግብር እንዲከፈል ማድረግ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ሰነዶች የተለያዩ ስርዓቶች /ፎርማሊቲዎች/ ባለማሟላታቸው ብቻ ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

የጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13065 በጥር 26 ቀን 1996 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.7813 በሐምሌ 16 ቀን 1995 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በግ/ይ/መ/ቁ. ው-17 በየካቲት 8 ቀን 1992 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

ግራ ቀኙ ወጪ እና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡